# ይ ር ጋ



የሰ/መ/ቁ/ 20295

ሐምሌ 5 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈስ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** አቶ ደጀኔ ለገሠ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ መላኩ ጌታቸው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የውርስ ሀብት ለመረከብ በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሳሽ በእናታቸው በወ/ሮ የልፍኝ እጅጉ ተተክተው የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ መሆናቸውን ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም በፍ/ቤት ውሳኔ አረጋግጠዋል፡፡ የተከሳሾች አያት ወ/ሮ ታደለች አርጋው ከወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ጋር በመሆን የአክስቴ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ ናቸው ተብሎ የካቲት 29 ቀን 1981 ዓ.ም በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ መቃወሚያ አቅርቤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም ተሰርዟል፡፡ ከዚያም ቤት ለማስለቀቅ ሚያዚያ 10 ቀን 1992 ዓ.ም በተከሳሾች እናትና በወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ላይ ክስ ብመሠርትም ተከሳሾች በሞት በመለየታቸው መጥሪያ ሳይደርሳቸው ክሱ ተቋርጧል፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሾች ከወ/ሮ ያምሮት እጅጉ የሚደርሰኝን የውርስ ሀብት ያስረክቡኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ ከሳሽ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ሕጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ያረጋገጡት ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ተከሳሾች

ይዘውብኛል የሚሉትን ቤት ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ያልጠየቁ ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000 (1) መሠረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት የከሳሽ ክስ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክሩን መርም [ ል፡፡

በዚህም መሠረት ከሳሽ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ መሆናቸውን ያረጋገጡት ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚህም በኂላም በተከሳሶቮች እናት ላይም ሆነ በተከሳሾች ላይ የውርስ ሀብት ይልቀቁልኝ በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እንዳገኙ ይቆጠራል፡፡

ይህ የይርጋ ጊዜ ሊቋረጥ ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ ክስ ቀርቦ በሆነ ጊዜ ሲሆን ከሳሽ በመ/ቁ 3311/81 የካቲት 29 ቀን 1981 ዓ.ም የተከሳሾች ወላጅ እናትና ወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ወራሾች ናቸው ተብሎ የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይህ የመቃወሚያ ክርክር የወራሽነት መብት ላይ ብቻ ያነጣጠረ በመሆኑና የውርስ ንብረት

ይሰጠኝ በሚል የቀረበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1851(ለ) መሠረት ይርጋው ተቋርጧል ለማለት አይችልም፡፡

ስለሆነም ከሳሽ የወራሽነት መብታቸውን ካረጋገጡና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሾች መያዛቸውን ካወቁ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ በተከሳሾች ላይ ክሱን ያላቀረቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ ቁጥር 1000(1) መሠረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተመሳሳይ ጭብጥ በመያዝ የፍ/ብ/ሕ ቁ.1000(1) ተፈፃሚነቱ አንድ የወራሽነት ማስረጃ ያለውና ነገር ግን ይህ ማስረጃው በሕግ ዓይን ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ውርሱን ወይም የውርሱን አንድ ክፍል የያዘ ከሆነ በሕጉ ዓይን



ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የያዘው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚጠየቅበት ጊዜ እንደሆነ በውሳኔው ላይ አስፍሮ በተያዘው ጉዳይ ግን መ/ሰጭዎች ተጠቃሹን ንብረት የያዙት ምንም ዓይነት የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖራቸው ስለሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ሳይሆን ቁጥር 1845 ነው ካለ በኂላ ከዚሁ አኳያ ሲታይም የይ/ባይ/የተጠሪ አውራሽ በ1978 ዓ.ም መሞታቸው የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪም በመብታቸው መሥራት የሚችሉት ከዚህ ጊዜ በኂላ ስለሆነ ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ክስ የመሠረቱት ምንም እንኳን መጥሪያው ለመ/ሰጭዎች አውራሽ ያልደረሰ ቢሆንም በ1992 ዓ.ም ከ14 ዓመት በኂላ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ላይ በተቀመጠው የ10 ዓመት ጊዜ ክሱ ያልቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ምክንያቱን ቀይሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወምና መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የመ/ሰጪዎች አውራሽ የሟች ወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ልጅ ነኝ በማለት ያወጡትን የወራሽነት ማስረጃ አመልካች ጥር 20 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መቃወሚያ በማቅረብ እንዲሰረዝ ካደረገ፣ የወራሽነት ማስረጃ ያሰረዘበት ውሳኔ ከግምት ሳይገባ ንብረቱን ለመረከብ የጠየቀው አውራሹ ከሞቱ ከ10 ዓመት በኂላ ነው ተብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው ክሱ በይርጋ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ አግባብነት በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን በሥር ፍ/ቤቶች በተጠሪ በኩል የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ ከአክስቴ ከወ/ሮ ያምሮት እጅጉ በውርስ የተላለፈልኝን ቤት ይዘው የሚገኙ ስለሆነ ያስረክቡኝ በማለት ነው፡፡

ተጠሪዎች የአመልካች አክስት የሆኑት የወ/ሮ ያምሮት እጅጉን ንብረት በመውረስ ረገድ የቅድሚያ መብት እንደሌላቸው ቢረጋገጥም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ይዘው የተገኙት ወራሽ ነን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በመውረስ ረገድ ከአመልካች የቀደመ መብት ባይኖራቸውም ንብረቱን ይዘው የሚገኙት የመውረስ መብት ሳይኖራቸው ነው ለማለት ግን የሚያስችል አይሆንም፡፡

ተጠሪዎች ቤቱን ይዘው የሚገኙት በወራሽነት መብት ነው ከተባለ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000(1) በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የይርጋ ክርክሩን ከቁጥር 1845 ድንጋጌ ጋር አያይዞ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ክሱ በይርጋ ተቋርጧል የሚል ውሳኔ የሰጠው ሕጉን በተገቢው ካለመተርጐም እንደሆነ ታምኖበታል፡፡በሌላ በኩልም አመልካች ተጠሪዎች የያዙትን የውርስ ንብረት ያስረክቡኝ በማለት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም ሲሆን የአክስታቸው ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት ደግሞ ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ነው፡፡

አመልካች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1000(1) ላይ የተቀመጠው የ3 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በተጠሪዎች ተይዞብኛል የሚሉት ንብረት እንዲመለስላቸው መጠየቅ ይገባቸው እንደነበር የሚታመን ከመሆኑም በላይ የተጠሪዎች አውራሽ የአመልካች አክስት ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ አመልካች ለማስረዝ አቤቱታ አቅርበው ክሱን ማቅረብ የሚችሉት ውሳኔው ከተሰረዘ በኋላ ነው ቢባል እንኳን ይሄው ውሳኔ በ1991 ዓ.ም ተሰርዞ ክሱን ግን ያቀረቡት የ3 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በ1996 ዓ.ም ስለሆነ ከተጠቀሰው የፍ.ብ.ሕ.ቁ 1000(1) አኳያ በይርጋ የማይታገድበት ምክንያት አልተገኘም፡



**ው ሳ ኔ**

(1) የሥር ፍ/ቤቶች የቀረበው ክስ በይርጋ ተቋርጧል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ሆኖ ስለተገኘ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
(2) የፍርዱ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ
(3) ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ
(4) መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

**ተጨማሪ ትዕዛዝ**

በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/09 የቤት ቁጥር 507 የሆነው ቤት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ባለበት ሁኔታ ተከብሮ እንዲቆይ በዚህ ፍ/ቤት በግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ በዚህ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ